**አብዮታዊ ዴሞክራሲ** (ጥር 10/1998 ቁጥር 199)


- በአበባ ምርት ከ150 ሚሊዮን ብር በላይ የውጭ ምንዛሪ ተገኘ - ገፅ 1
- የደኢህዴን ማዕከላዊ ኮሚቴ ውሳኔዎችን አሳለፈ - ገፅ 2
- በአማራ ክልል 248 ሺህ ሄክታር በዘር ይሸፈናል - ገፅ 4
- የስድስት ወራት ትርፎች - ገፅ 5
- የተሳሰሩ ተግባራትን ለተፋጠነ ዕድገት - ገፅ 7
- የዘንድሮውን ምርት ለበግል ስራ ዝግጅት - ገፅ 8
- እኛ ለህግ የበላይነት እነሱ ከህግ በላይ ለመሆን - ገፅ 11


**ዜና**

## በአበባ ምርት ከ150 ሚሊዮን ብር በላይ የውጭ ምንዛሪ ተገኘ

የኢትዮጵያ አበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ አምራቾች ማህበር በተጠናቀቀው የፈረንጆች አመት ወደ ውጭ ከተላከው የአበባ ምርት ከ150 ሚሊዮን ብር በላይ የውጭ ምንዛሪ መገኘቱን አስታወቀ።

የማህበሩ ሊቀመንበር አቶ ፀጋዬ አበበ ለጋዜጣው ሪፖርተር እንደገለፁት፣ የማህበሩ አባላት በሆኑት 45 አበባ አምራች ባለሃብቶች ወደውጭ ከተላከ የአበባ ምርጥ በተጠናቀቀው የፈረንጆች አመት ከ150 ሚሊዮን ብር በላይ የውጭ ምንዛሪ ተገኝቷል።

የአበባ ምርቱ በብዛት የሚላከው ወደ ሆላንድ መሆኑን የገለፁት አቶ ፀጋዬ በተጨማሪም ወደ እንግሊዝ፣ አሜሪካ፣ መካከለኛው ምስራቅ፣ አረብ አገሮች እንዲሁም ወደተለያዩ የአፍሪካ ከተሞች መላክ በቅርቡ እንደተጀመረ ተናግረዋል።ምርቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተቀባይነትን በማግኘቱ የሚላከው ምርት ብዛት እየጨመረ መምጣቱን አቶ ፀጋዬ ጠቁመው፣ የማሸጊያና የማስቀመጫ ደረጃ ማሻሻል አስፈላጊ መሆኑንም ገልፀዋል።

ዘርፉ ለአገር ኢኮኖሚ አጋዥ ከመሆኑ በተጨማሪ ከ16 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ሰዎች የስራ ዕድል መፍጠሩንም አቶ ፀጋዬ ገልፀዋል። መንግስት ለዘርፉ መስፋፋት የሚያደርገው እገዛ አበረታች መሆኑን አቶ ፀጋዬ ተናግረው በቅርቡ ከጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ጋር ተካሂዶ የነበረው ውይይት በዘርፉ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት አስተዋፅኦ ማድረጉን ጠቁመዋል።

ለዘርፉ ከእርሻ ኮሌጅ ተምረው የሚወጡት ባለሙያዎች በጠቅላላ እርሻ ላይ የሰለጠኑ በመሆናቸውና በዘርፉ ለማገልገል ተቸግረው እንደነበር አቶ ፀጋዬ አስታውሰው በቅርቡ በአበባ ምርት አጭር ስልጠና በመስጠት ለችግሩ መፍትሄ ማግኘት መቻሉን አስረድተዋል። ወደፊት በዘርፉ የሚታዩ ችግሮችን በመ ፍታትና ወቅታዊ የሆኑ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በመጠቀም በዘርፉ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪ በ2006 በእጥፍ ለማሳደግ መታቀዱን ከአቶ ፀጋዬ ገለፃ ለመረዳት ተችሏል።

# የደኢህዴን ማዕከላዊ ኮሚቴ ውሳኔዎችን አሳለፈ

የደኢህዴን ማዕከላዊ ኮሚቴ ባለፉት ስድስት ወራት የተሳኩ ያከናወናቸውን ተግባራት በመገምገምና የቀጣዮቹ ወራት የትኩረት አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ ልዩ ልዩ ውሳኔዎችን ማሳለፉ ተገለፀ፡፡

የንቅናቄው ፅ/ቤት እንደገለፀው ማዕከላዊ ኮሚቴው ባለፈው ሳምንት ባካሄደው መደበኛ ስብሰባ ህዝቡ በምርጫ የሰጠው ስልጣን መሰረት አድርጎ በየደረጃው መንግስታዊ መዋቅሮችን የመዘርጋት፣ የጎዳና ላይ ነውጥን የመግታትና ስልጠናን ማዕከል ያደረገ የህዝብ ግንኙነትና የድርጅት ስራ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ገምግሟል፡፡

በዚህም መሰረት ከክልል ጀምሮ እስከ ወረዳ ድረስ ብቃት ባላቸው አባላት መንግስታዊ መዋቅር በመዘርጋቱ በቀጣይ ለሚካሄዱ የልማትና የመልካም አስተዳደር ተግባራት ምቹ ሁኔታ መፈጠሩን አረጋግጧል፡፡

በምርጫ ህዝብ የሰጠውን ብያኔ ለመቀበል የተሳናቸውን አክራሪ የተቃዋሚ አመራሮች የከፈቱት የጎዳና ላይ ነውጥ የክልሉ ህዝብ በወሰደው የፀና አቋም የከፋ ጉዳት ሳያስከትል በእንጭጩ እንዲቀጭ መደረጉም አበረታች ተግባር መሆኑን ጠቁሟል፡፡

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች በክረምት ወራት ያደረጉት ውይይት በስሜት በመነሳት የጥፋት ሃይሎች መሳሪያ ከመሆን የታደጋቸው ከመሆኑም በላይ የተቋማቱን ፖለቲካዊ ሁኔታ ከመሰረቱ የለወጠና ጤናማ ውጤት የተገኘበት መሆኑን ማዕከላዊ ኮሚቴው አረጋግጧል፡፡

ለገጠር ልማት ባለሙያዎች የተሰጠው ስልጠና በገጠር ልማት ፖሊሲዎች አፈፃፀም ረገድ ይከሰቱ የነበሩትን የአመለካከትና የአፈፃፀም ችግሮችን ለመቅረፍ ከፍተኛ እገዛ ማድረጉ ተጠቁሟል፡፡

እንዲሁም የአርሶ አደሮችና የአርብቶ አደሮች ስልጠናዎችም ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ግልፅና ነፃ ውይይቶች የተካሄደበት ከመሆኑም በላይ ጥገኝነትን በመታገል የስራ ተነሳሽነትን የፈጠረለት መሆኑ በግምገማው ተረጋግጧል፡፡

በአጠቃላይ በተሰጡት ስልጠናዎች ከሶስት መቶ ሺህ በላይ አዳዲስ አባላትን ማፍራት መቻሉ የንቅናቄውን ማህበራዊ መሰረት በማስፋት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማበርከቱ የስራ አፈፃፀም ግምገማው አመልክቷል፡፡

ባለፉት ስድስት ወራት የተከናወኑ ተግባራት በክልሉ መልካም አስተዳደርን በማስፈን ልማትን ለማፋጠን ምቹ ሁኔታዎች መፈጠራቸውን ያረጋገጠው የማዕከላዊ ኮሚቴው ግምገማ በቀጣይ ርብርብ ሊደረግባቸው የሚገቡ አቅጣጫዎችን ማስቀመጡን ፅ/ቤቱ አስረድቷል፡፡

በዚህም መሰረት በጎዳና ላይ ነውጥ ምክንያት ተፅዕኖ ያረፈበትን የልማት ስራ ለማካካስና መልካም አስተዳደርን የማስፈን ተግባር በቀጣዮቹ ወራት ሰፊ ትኩረት ተሰጥቶ መፈፀም እንዳለበት ጠቁሟል፡፡

በክልሉ የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ፣ ምርታማነትን ለማሳደግ በተለይም ለወጪ ንግድ የሚሆኑ ሰብሎችን በስፋት ለማምረት በየደረጃው ጥረት እንዲደረግ ማዕከላዊ ኮሚቴው አሳስቧል፡፡

መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የሚያስችል የአመራር ስልጠና መስጠት እንዳለበት ያመላከተው ማዕከላዊ ኮሚቴው በየደረጃው የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርምን ተግባራዊ በማድረግ በኩል የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመቅረፍ እንቅስቃሴ እንዲደረግ አመልክቷል፡፡

እንዲሁም በንቅናቄው ህገ ደንብ መሰረት የድርጅት ጉባኤ ማካሄድ የነበረበት ቢሆንም የተጀመሩ ተስፋ ሰጪ እንቅስቃሴዎች መልክ እንዲይዙ ተደርጎ ከስድስት ወራት በኋላ ጉባኤው እንዲካሄድ በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው በኩል የቀረበውን ጥያቄ ተቀብሎ አፅድቆታል፡፡

ለጉባኤው መሳካት ከወዲሁ ዝግጅት እንዲካሄድም የጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴ አባላትን ስራ አስፈፃሚው ሰይሞ እንዲንቀሳቀስ ሃላፊነት የሰጠ ሲሆን፣ በትምህርት ምክንያት ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በለቀቁት በአቶ ፊሊሞን ሐዳሮ ቦታ ዶ/ር ሽፈራው ተክለማርያምን መርጧል፡፡

በቀጣዮቹ ወራት የሚካሄዱ የልማትና የመልካም አስተዳደር ተግባራት የህዝቡን ኑሮ በማሻሻል ትርጉም ያለውን ለውጥ ለማምጣት እንዲችሉ በየደረጃው ያለው አመራር፣ አባላትና ህዝቡ የበኩላቸውን ርብርብ እንዲያደርጉም ጥሪ አስተላልፏል፡፡

# በአማራ ክልል 248 ሺህ ሄክታር በዘር ይሸፈናል

በአማራ ክልል በልግ አብቃይ በሆኑ አራት ዞኖች 248 ሺህ ሄክታር መሬት በተለያዩ አዝርዕቶች እንደሚሸፈን የክልሉ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ አስታወቀ።

በቢሮው የሰብል ልማትና ጥበቃ መም ሪያ ተወካይ አቶ ሺመላሽ የሻነ ሰሞኑን ለጋዜ ጣው ሪፖርተር እንዳስታወቁት በልግ አብቃይ በሆኑ በሰሜን ሸዋ፣ ደቡብ ወሎ፣ ሰሜን ወሎ እና ኦሮሚያ ዞኖች 248 ሺህ ሄክታር መሬት በበቆሎ፣ ስንዴና ማሽላ ዘሮች ይሸፈናል።

ከዚህም በዘር ከሚሸፈነው መሬት 4 ሚሊዮን 200 ሺህ ኩንታል ምርት ለማግኘት መታቀዱን ተወካዩ ተናግረዋል።

አርሶ አደሩ በአሁኑ ወቅትከሰብል ነፃ የሆነውን መሬት በማረስ ሂደት ላይ መሆኑን የገለፁት አቶ ሺመላሽ እስካሁንም 49 ሺህ 783 ሄክታር መሬት ታርሶ ለዘር መዘጋጀቱንና ሰብል ባልተሰበሰበባቸው አካባቢዎችም በአፋጣኝ ሰብስቦ መሬቱን ለዘር ማዘጋጀት ይጠበቅበታል ብለዋል።

ቢሮው ለበልግ የእርሻ ወቅት የሚውል 12 ሺህ 970 ኩንታል ዳፕ እና 6 ሺህ 530 ኩንታል ዩሪያ ማዳበሪያ ማቅረቡን የጠቀሱት ተወካዩ ከዚህ በተጨማሪም አርሶ አደሩ 16 ነጥብ 8 ሚሊዮን ኩንታል የተፈጥሮ ማዳበሪያ እንዲጠቀም ዝግጅት እየተደረገ ነው ብለዋል።

የተፈጥሮ ማዳበሪያ የመሬትን ለምነት በመጠበቅ ምርታማነትን የሚጨምር በመሆኑ በአርሶ አደሩ ዘንድ ተቀባይነት እያገኘ በመምጣቱ በስፋት ለመጠቀም በቂ የተፈጥሮ ማዳበሪያ መኖሩን አስረድተዋል።

ከዚህ በተጨማሪ ለማረስ ምቹ የሆኑ የሐረር አካፋና ታይሪጀር የተባሉ ዘመናዊ ማረሻዎች እንዲጠቀም አስፈላጊው ትምህርት እየተሰጠ መሆኑን ከተወካዩ ገለፃ ለመረዳት ተችሏል።

# የስድስት ወራት ትርፎች

የደቡብ ኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰ ቦችና ህዝቦች ክልል መሪ ፓርቲ ደኢህዴን/ኢህአዴግ ባለፈው ሳምንት የማዕከላዊ ኮሚቴው የግማሽ አመት የስራ አፈፃፀም ሪፖርትና የቀጣዩ ስድስት ወር የትኩረት አቅጣጫ ላይ ውይይት አድርጎ ነበር።

የ1998 የበጀት አመት የመጀመሪያው ግማሽ አመት በመሰረቱ እንደ መሪ ፓርቲም ሆነ እንደ ክልል አስቀድመው የታቀዱ ተግባራት ብቻ አይደሉም የተከናወኑት። ሶስተኛውን ዙር አገር አቀፍ ምርጫንና ውጤቱን ተከትለው ፀረ ሰላም ሃይሎች የፈጠሯቸው የሁከትና ነውጥ ሙከራዎችን ለማክሸፍ የተከናወኑ ስራዎች በማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ተገምግሟል።

ከምርጫው ጋር ተያይዘው ይከሰቱ የነበሩ ሁከትና ነውጦችን የመግታት፣ የክልሉ ህዝብን ሰላም የማስጠበቅ፣ ህዝቡን በማወያየት ሁከቶቹን ተከትለው የተፈጠሩ አለመረጋጋ ቶችን በማስተካከል የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ በስፋት ተከናውነዋል። የደኢህዴን ማዕከላዊ ኮሚቴ ከሃምሌ 1997 አንስቶ ዋና ስራ ሆኖ የሰነበተው ይኸው የማረጋጋትና በተጓዳኙ የተካሄደ ሰፊ የስልጠና ስራ መሆኑን ነው ያስመረበት። የፀረ ሰላም ሃይሎች የሁከት ተግባር በመንግስታዊ የልማትና የመልካም አስተዳደር ስራዎች አተገባበር ዘገምተኛ አድርጎ የሰነበተ መሆኑን የንቅናቄው ማዕከላዊ ኮሚቴ በውል ያጤነው ሲሆን በዚህ ረገድ የባከነውን ጊዜ በሚያካክስ መልኩ ሁለተኛውን ግማሽ አመት በተገቢው መጠቀምን ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫው አድርጎም ተስማምቶበታል።

የንቅናቄው ማዕከላዊ ኮሚቴ መስከረም ወር ላይ ባደረገው ስብሰባ የህዝብ ግንኙነትና የድርጅት ዘርፍ አቢይ ተግባር የስልጠና ስራ መሆን እንዳለበት የወሰነ ሲሆን በዚህ በመንፈቅ አመት አፈፃፀም ሪፖርቱ ውይይት ላይ ይህን በተመለከተም ትኩረት ሰጥቶ ተመልክቶታል። በዚህም መሰረት ባለፈው ክረምት በሁለት ዙር የተሰጠውን የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችንና ወጣት ምሁራንን ስልጠና ተገቢነት ከወዲሁ ከተገኘ መልካም ውጤት ጋር አያይዞ አዎንታ ዊነቱ ላይ ተነጋግሯል። በቀጣይ መንፈቅም በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ከሁለተኛ ደረጃ እስከ ኮሌጆች ባሉ የትምህርት ተቋማት የሚገኙ ተማሪዎች ስልጠና የማግኘታቸው ጉዳይን እንደ አንድ ተግባር አድርጎም በመውሰድ የንቅናቄው ከፍተኛ አመራር ተቀብሎታል።

የክልሉ የገጠርና የግብርና ልማት ባለሙያዎች ከገጠሩ ህዝብ ጋር በመሆን የገጠር ልማት ፖሊሲን በማስፈፀም ረገድ የታየባቸውን የአፈፃፀምና የአመለካከት ችግር መሰረት ያደረገ የፖሊሲ ስልጠና በሁለት ዙር ተሰጥቷቸው ነበር። የጉራጌ ዞንን ሳይጨምር በሁሉም ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች የሚገኙትን የገጠር ልማት ባለሙያዎች ለ21 ቀናት በፖሊሲዎች ላይ እንዲሰለጥኑ ተደርጓል። 10 ሺህ 913 ባለሙያዎች እንዲሰለጥኑ ታቅዶ 10 ሺህ 866 ባለሙያዎች ሰልጥነዋል። ይህ ደግሞ የዕቅዱ 99 በመቶ ማለት ነው። የደኢህዴን ማዕከላዊ ኮሚቴ ከገጠር ሙያተኞች ውስጥ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችን በቅርብ ጊዜ ለማሰልጠን የተደረገውን ቅድመ ዝግጅት በተገቢው መርምሮ ይኸው ስልጠና የግብርና ባለሙያዎች በሰለጠኑበት መንገድ እንዲፈፀምም ወስኗል።

ደኢህዴን ከበጀት አመቱ የመጀመሪያ መንፈቅ ተግባራቱ በዝግጅቱም ሆነ በስልጠና አግባብ «የስልጠናዎችም ሆነ የተግባራት አውራ» አድርጎ የተንቀሳቀሰው አርሶ አደሮችንና አርብቶ አደሮችን በማሰልጠን ነበር። በዚህ ስልጠና በ15 ቀናት ውስጥ ከ450 ሺህ በላይ አርብቶ አደሮችንና አርሶ አደሮችን ማሰልጠን ችሏል። የሰልጣኞች ጥንቅር እድሜንና ጾታን ያካተተና በምግባራቸው ግንባር ቀደም የሆኑትን ያካተተ ሲሆን የሰልጣኞች አመራረጥም በህዝብ ተሳትፎ የተከናወነ ነበር። የስልጠናው አጀንዳ ከአርሶ አደሩ ህይወትና ከአካባቢው መለወጥ ጋር የተቆራኘ ሆኖ መቅረቡን፣ ሰልጣኙ ሃይልም ስሜቱን ሳይደብቅ

እየተከራከረና እየተወያየ የጋራ መደምደሚያዎች ላይ የደረሰ መሆኑን የንቅናቄው ማዕከላዊ ኮሚቴ ተመልክቶታል፡፡

ደኢህዴን/ኢህአዴግ በመጀመሪያ ግማሽ አመት ያከናወናቸው ባለ ሶስት ምዕራፍ የስልጠና ስራዎች በገጠር የደኢህዴን/ኢህአዴግ የሰላም፣ የዴሞክራሲና የልማት መስመር ወገንተኛ የሆነ ሰፊ ሃይል ፈጥሯል፡፡ በዩኒቨርስቲዎች ውስጥ ደግሞ ለአመፅና ለስሜታዊ መነሳሳት በቀላሉ የማይበገር እንዳለፈው ጊዜ እየተደናገረ ከመቀላቀል የተቆጠበ፣ አመፅን በተጨባጭ የሚቃወም፣ ህገ መንግስታዊ ስርአቱን ከአደጋ የመከላከል አስፈላጊነትን በጥብቅ ማመን የጀመረ ሃይል ለማፍራት ተችሏል፡፡

በእነዚህ የክልሉ የግማሽ አመት አበ ይት የስልጠና ስራዎች አብረው ሊታቀፉ ባልቻሉ አካባቢዎች (ለምሳሌ የጉራጌ ዞን) አካባቢዎች የመጀመሪያው ምዕራፍ (የግብርና ባለሙያዎች ስልጠና) በዞኑ ሁለት ማዕከላት የተጀመረበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡

ደኢህዴን/ኢህአዴግ ባለፉት ስድስት ወራት ባከናወኗቸው አበይት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች የመንግስትን ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በተሻለ መልኩ የተገነዘበ፣ የትኛውም የሁከትና የአመፅ ሃይል በሚዘረጋው የስሜት ወጥመድ ውስጥ በጭፍኑ የማይገባ ሃይል ፈጥሯል፡፡ በተያያዘ ሁኔታም የተገኙትን ድሎች በትኖ ጥቅሙን ተፃርሮ የማይቆም ሃይል ከመገንባት አንፃር ትምክህትን፣ ጠባብነትንና በጥቅሉ ጥገኝነትን በአስተማማኝ መልኩ የሚታገል ጠንካራ የሰላም፣ የዴሞክራሲ፣ የልማትና ለዴሞክራሲያዊ አንድነት የቆመ ሃይል አጠናክሯል፡፡ በአጠቃላይ ስልጠናዎቹ ፋይዳ ያላቸው፣ ፋይዳቸውም ከወዲሁ በግልፅ መታየት ጀምሯል፡፡

ከዚህ አንፃር የመጀመሪያው ግማሽ አመት መሰራት የነበረባቸው የልማትና የመልካም አስተዳደር ስራዎች፣ ከሁለተኛው ግማሽ አመት ተግባራት ጋር ተካክሰውና ተስማምተው መሰራት እንደሚገባቸው የስልጠና ስራዎችም በተጓዳኙ ተጠናክረው መቀጠል እንደሚገባቸው ይጠበቃል፡፡ የክልሉ መሪ ፓርቲ ደኢህዴን/ኢህአዴግ የስድስት ወር የስራ አፈፃፀምና ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች ላይ ያደረገው ውይይት መደምደሚያም ይኸው ነው፡፡

## ርዕሰ አንቀፅ

# የተሳሰሩ ተግባራትን ለተፋጠነ ዕድገት

አሁን ባለንበት ወቅት በገጠር አካባቢ ሁለት መሰረታዊ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ በአንድ በኩል ምርትን የመሰብሰብ ተግባር ሲሆን በሌላ በኩል የበልግ ስራ ዝግጅት ነው፡፡

የዘንድሮ ምርት የተሻለ ሊሆን ይችላል የሚል አስተያየት በተለያዩ አካላት እየተሰጠ ነው፡፡ የዘንድሮ ምርት የተሻለ የመሆኑ ጉዳይ በዳታ ተደግፎ በግልፅ መቀመጥ ሲችል ለመረዳትም ይሁን ለማነፃፀር የበለጠ የሚረዳ እንደሆነ ግልፅ ቢሆንም የተሻለ ውጤት እንዳለው ግን ከተገኙት መረጃዎች በመነሳት መገመት ይቻላል፡፡

በምርት አሰባሰቡ ሂደት የመጀመሪያው ትኩረት የሚሰጠው ሰብሉን በአግባቡ የመሰብሰብ ጉዳይ ላይ ነው፡፡ ብክነትን፣ ብልሽትን፣ መከላከልና በጥንቃቄ መሰብሰብም ያስፈልጋል፡፡ ከዝግጅት ጀምሮ የተደከመበት ምርትን ካለምንም ብልሽትና ብክነት ሰብስቦ ለሌላ ውጤት ማብቃት ካልተቻለ ዋጋ የለውም፡፡

አርሶ አደሩ ባካሄዳቸው የተለያዩ ኮንፈረንሶች እንደተገለፀው ተዝካርና ሰርግ በማድረግ ምክንያት ፈልጎ በመደገስ ጭምር የተገኘን ምርት፣ ጊዜና ጉልበትን ያላግባብ ከማባከን ጋር የሚያያዝ አስተሳሰብ በስፋት እንዳለ ተወስቷል፡፡ የተለየው ነገር በዘንድሮው ኮንፈረንስ በዛ ያሉ ጉዳቱን ያስተዋሉ አርሶ አደሮች በተግባር ለውጥ በማየታቸው ምሳሌ ለመሆን በቅተዋል፤ ይህንንም መሰረት አድርገው ሌላውን ማስተማር ጀምረዋል፡፡ በመሆኑም በኮንፈረንሱ የተላለፈው ብክነትን የመከላከል ውሳኔ ተግባራዊ መሆን ይኖርበታል፤ ምርትን ለፍጆታ የመጠቀም ጉዳይ አግባብና በእቅድ የተደገፈ አካሄድን ሊከተል ይገባል፡፡ እህሉ ለገበያ ቀርቦ የሚገኝ ገንዘብም መሰረታዊ ለውጥን በሚያረጋግጡ ተግባራት ላይ መዋል ይኖርበታል፡፡

በተለይም ደግሞ ወቅቱ የበልግ ስራ ዝግጅትና ተግባር የሚከናወንበት በመሆኑ የምርቱ ውጤታማነት ወደ በልግ ስራ እንዲያሸጋግር መምራት ይገባል፡፡ አርሶ አደሩ ያለችግር የበልጉን ስራ ወደማፋጠንና ወደማሳካት እንዲጓዝ ጎጆን ለማቅናት አገርን ለተሻለ እድገት ለማብቃት ይረዳልና ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

እነዚህ ተግባራት በአርሶ አደሩ በኩል ትኩረት በተሰጣቸው ቁጥር ወደ ከተማ ለሽያጭ የሚወጣው እህል ብዛት ስለሚኖረው ዋጋው ተመጣጣኝ ይሆናል፤ የኑሮ ውድነትም ይረግባል፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ከግብርና ምርት ጋር ትስስር ያላቸው ፋብሪካዎች የተሻለ ጥሩ አቅም ስለሚያገኙ ምርታቸው ሳይስተጓጎል እንዲካሄድ ይረዳል፡፡

ከዚህም አልፎ መንግስት የሚያከናውናቸው ተግባራት ተስተካክለው በተረጋጋ መንገድ እንዲሄዱም ያግዛል፣ ልማት በተረጋገጠ ቁጥር ተረጋግቶ የሚወያይ፣ በስፋት ወደ ስራ የሚሰማራ የሰው ሃይል ይኖራል፡፡ የመንግስት ገቢ ስለሚጨምር የሃገሪቱ ዕድገት ይፋጠናል፡፡

በአጠቃላይ ይህ እንደ ሰንሰለት የተሳሰረ ለውጥ ሳይደናቀፍና መሃል ላይ መቆራረጥ ሳይገጥመው እንዲከናወን በስራው ላይ የሚሰማሩት አርሶ አደሮች ትኩረት የላቀ ሊሆን ይገባል፡፡ የቅርብ ድጋፍ የሚሰጡት ባለሙያዎችም ከእርሻው ሳይነጠሉ ድጋፋቸው ሊጠናከር ይገባል፡፡ በየደረጃው ያሉ የአመራር አካላትም መፈታት ያለባቸውን ችግሮች በፍጥነት እየፈቱ ተሳስረው መምራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

## ትኩረት

# የዘንድሮውን ምርት ለበግል ስራ ዝግጅት

የአርሶ አደሩ ጉልበት፣ መሬትና ውሃ አስተባብሮ በመጠቀሙ በየጊዜው ትልልቅ ዕድገቶች እየተመዘገቡ ይገኛሉ። በተለይም ደግሞ ገጠርንና አርሶ አደሩን ማዕከል ያደረገው ፖሊሲና ስትራቴጂ ከተቀየሰ በኋላ ሁለገብ የሆነ ዕድገትን ማስመዝገብ ተችሏል።

ከ1984 ዓ.ም በፊት ባሉት 10 አመታት የሃገር ውስጥ ምርትና የህዝብ ዕድገትን አነፃፅሮ በመነሻነት ማየት ይቻላል። በነዚህ አመታት አማካኝ የምርት ዕድገት 1 ነጥብ 9 በመቶ ሲሆን የህዝብ ዕድገትም 3 በመቶ ነበር። ይህ ዳታ የነፍስ ወከፍ ገቢን ወደ 1 ነጥብ 1 በመቶ ዝቅ እንዲል አድርጎታል። ከ1985 እስከ 1996 ባሉት አመታት ደግሞ አማካኝ የምርት ዕድገት 5 ነጥብ 1 ከመቶ ነበር። በነዚህ አመታት ግብርና 2 ነጥብ 9 በመቶ፣ ኢንዱስትሪ 7 ነጥብ 2 በመቶ አገልግሎት 7 ነጥብ 7 በመቶ እንደነበር መረጃዎች ያመለክታሉ። በወቅቱ የነበረው የህዝብ ዕድገት 3 በመቶ በመሆኑ የነብስ ወከፍ ገቢን ከሚያሽቆለቁልበት ፍጥነት ተገትቶ 2 ነጥብ 1 አመታዊ ዕድገትን ማስመዝገብ ተችሏል።

ከተሃድሶ ወዲህ በተለይም በ1996 እና 1997 ዓ.ም የምርት ዕድገት ወደ 10 በመቶ ያደገ ሲሆን፣ የነብስ ወከፍ ገቢንም 7 በመቶ ማሳደግ ተችሏል። በተለይ በዚህ ወቅት የነበረውን ከፍተኛ ድርቅና ከሻዕቢያ ጋር የነበረውን ጦርነት በመሸከም ይህ ዕድገት መመዝገቡ ሃገራችን ምን ያህል በተስተካከለ አቅጣጫ የሚጓዝ ፖሊሲና ስትራቴጂ እንደነበረ ማመላከቻ ነው።

ይህ ከላይ የተገለፀውን በየጊዜው እያደገ የሄደውን ለውጥ ለማረጋገጥ በተለይ ኢህአዴግ በሚመራቸው ክልሎች የተለያዩ ዕቅዶች እየወጡ እንቅስቃሴ ተደርጓል። በተለይም የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ውሃን ማዕከል ያደረጉ ተግባራት እንዲከናወኑና አርሶ አደሩ የአመቱን አብዛኛዎቹን ቀናት በስራ እንዲያሳልፍ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል።

ለምሳሌ በአማራና በደቡብ ክልሎች የነበረውን ስራ በተወሰነ ደረጃ በምሳሌነት ማንሳት ይቻላል። በአማራ ክልል በ1997 የነበረው 69 ሺህ ሄክታር ነባር መሬት ላይ 170 ሺህ ሄክታር በመጨመር ለማልማት ዕቅድ ተይዞ ነበር። ከዚህ ውስጥ በስድስት ወራት ብቻ 94 ሺህ 371 ሄክታር (39 ነጥብ 5 በመቶ) በመስኖ ልማት ለመሸፈን ተችሏል።

በደቡብ ክልል ደግሞ በ1996 ዓ.ም የተገነቡ ገንዳዎችን ጨምሮ በሁሉም አይነት የውሃ ማጠራቀሚያዎች በመጠቀም 2 ሺህ 144 ሄክታር መሬት በተለያዩ ሰብሎች ለምቶ 146 ሺህ 204 ኩንታል ምርት ተገኝቷል።

እነዚህ ከላይ የተገለፁት የተወሰኑ ዳታዎች የሚያመላክቱት በየጊዜው ውሃን ከሰማይ አንጋጦ በመጠበቅና የክረምት ወራትን ብቻ በማየት ብቻ ሳይሆን የከርሰ ምድር ውሃን ቆፍሮ በማውጣት፣ አልፎ ሂያጅ ወንዝን በመጥለፍ፣ ጎርፍን በመቀልበስ፣ በመሳሰሉት ያለውን የውሃ ሃብት በአግባቡ መጠቀም እንደሚቻል ነው።

ይህንን ለማድረግ የመጀመሪያውና ግልፅ ነገር ሃገሪቱ የምትመራበት የግብርና ፖሊሲና ስትራቴጂ ላይ የሚመሰረት ቢሆንም ይህንን ወደ ተግባር ለመቀየር የየአካባቢውን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ ዕቅድ መንደፍ መቻል ነው። በመሆኑም በየክልሉ ብቻ ሳይሆን እስከ ወረዳ ድረስ፣ የመሬቱን አይነትና ስፋት፣ የህዝቡን ፍላጎትና አቅም፣ የአካባቢ ውን የተፈጥሮ ሃብት ሁኔታ፣ የመሳሰሉትን በማገናዘብ እቅድ ማውጣት ተችሏል።

ከእቅዱ ጋር በተያያዘ አርሶ አደሩ ይሁን በቅርብ የሚመለከታቸው አመራሮችና እና ባለሙያዎች እንዲያምኑበት የማድረግ ስራ ነው። ከአመት አመት ካልተሰራ በስተቀር እቅዱን ውጤታማ ማድረግ

አይቻልም። በመሆኑም አርሶ አደሩ በበአላት ሳያባክን ክረምትን ሳይጠብቅ መስራት እንደሚችል ማሳየት፣ የውሃ አጠቃቀም ሁኔታውን የሚያስተካክልበትን ሁኔታ ማመላከት፣ ጉልበቱ ሳይባክን እንዴት ውጤታማ በሆነ መንገድ መስራት እንዳለበት ማስገንዘብ፣ መሬቱን በየወቅቱ ለማልማት መስነፍ እንደሌለበት ማስረዳትና የመሳሰሉት ስራዎችን ማከናወን በቀላሉ የሚታዩ አይደሉም።

አርሶ አደሩ ያላመነበትን ስራ መስራት ስለማይቻልና ይህ በሆነ ቁጥር ደግሞ ፈጣን ዕድገትን ማስመዝገብ የሚታሰብ ነገር ባለመሆኑ ኮንፈረንሶችን ከማዘጋጀት ጀምሮ በየአካባቢው ባሉ የግብርና ባለሙያዎችና የልማት ቡድኖች ከፍተኛ ስራ ተሰርቷል። አርሶ አደሩ በሚያመጣው የአስተሳሰብ ለውጥና በሚፈጥረው የባለቤትነት መንፈስ አማካኝነትም የሚታይ ለውጥ ማረጋገጥ ተችሏል።

ይህ የአስተሳሰብ ለውጥ ያረጋገጠው ውጤት በየጊዜው ከሚኖረው ተግባር ጋር እየተቆራኘ እንዲከናወን ማድረግ ያስፈልጋል። ለምሳሌ አሁን ባለንበት ወቅት ሁለት ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛሉ። በአንድ በኩል በጥሩ ሁኔታ ላይ የሚገኘውን ሰብል የመሰብሰብ ተግባር ሲሆን በሌላ በኩል የበልግ ስራዎች የሚከናወን ተግባር ነው።

ሰብሉን የመሰብሰብ ሁኔታ በብቃት መከናወን ያለበት ነው። ከብክነት የመከላከል ጉዳይ ተያይዞ የሚነሳ ነገር ነው። በአሁኑ የምርት ዘመን በዳታ የተደገፈው መረጃ ገና ያልተጠናቀረ ቢሆንም በብዙ ባለሙያዎች አስተያየት የተሻለ ምርት ተገኝቷል ተብሎ ይገመታል። ይህን የተሻለ ምርት በጥንቃቄና በአግባቡ መጠቀም ይገባል።

ምርቱ ሳይባክን በባለሙያዎች እየታገዙ መሰብሰብ አንድ ነገር ሆኖ በስፋት ምርት ተገኝቷልና ብሎ ማድፋፋትም አይገባም። በብዙ ጥረትና ልፋት የተገኘውን ምርት ለሰርግ፣ ለተዝካር ማውጣትና ማባከን ጉዳቱ ከፍተኛ ነው። ይህ በተካሄዱት ኮንፈረንሶች ሁሉ የተወገዘና አርሶ አደሩም እንዲህ አይነት ስህተት ላለመስራት ቃል የገባበት ነው። በመሆኑም ምርቱን በአግባቡ ይዞ ቆጥቦ መጠቀምና ህይወትን በሚቀይሩ፣ ጎጆን በሚያቀኑ ተግባራት ላይ በማዋል የማያቋርጥ ዕድገትን ማስመዝገብ ይገባል። የኮንፈረንሶቹ ውሳኔ በተግባር መጠበቅ ይኖርበታል።

በሌላ በኩል የትናንቱን ድርቅና የሚያጋጥመውን ችግርም መዘንጋት አያስፈልግም። ጥሩ ምርት ስለተገኘ እስኪያልቅ ድረስ እጅና እግርን አጣጥፎ መቀመጥ መታሰብ የለበትም። ወቅቱ የበልግ ስራ ዝግጅትና የመስኖ ልማት የሚከናወንበት ወቅት ነው። ከየአካባቢው ሁኔታ ጋር በተናዘበ አኳኋን በበልግ የሚዘሩ ሰብሎችን መለየት፣ ዘር ማዘጋጀት፣ በበልግ የሚዘራውን ማሳ በወቅቱና በጥራት ማረስና ማለስለስ፣ የጥቁር አፈር ውሃ በማጠንፈፍ ለመጠቀም የመያስችል ዝግጅት ማድረግና የመሳሰሉት ስራዎች ማከናወን ይገባል።

እንደበልጉ ስራ ሁሉ የመስኖና የውሃ ማሰባሰብ ስራዎች አሁን በማሳ ላይ ያለው ምርት እንደታጨደ ፈጥነው መጀመር አለባቸው። በአመት ሁለቴና ሶስቴ ማምረት የሚቻለው በዋነኛነት የመስኖ ስራ በመስራት ነው። ባህላዊ መስኖዎችን በስፋት መጠቀም፣ ቀደም ብለው የተጀመሩና ሊጠገኑ የሚገባቸውን መጠገን፣ አዳዲሶችን መስራት ያስፈልጋል።

በሌላ በኩል በክረምት የተሰባሰበን ወይም ደግሞ አምና ተቆፍሮ የወጣን ውሃ በመጠቀም ለገበያ የሚቀርብ ምርት ማምረት ይገባል። በቂ እርጥበት ባለባቸው አካባቢዎች የከርሰ ምድር ውሃ ጉድጓድ ቆፍሮ በማውጣት በእርጥበት አጠር አካባቢዎች ደግሞ የተለያዩ የውሃ ማሰባሰብ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም እያንዳንዱ አርሶ አደር በማሳውና በጓሮው ውሃ እንዲኖረው ለማብቃት ሰፊ የማነሳሳት ስራ መስራት የማይታለፍ ተግባር ይሆናል።

ከላይ የተገለፁት ምርትን በአግባቡ የማሰባሰብና የበልግ ስራን የማከናወን ተግባራትን የመጀመር ጉዳይ ወቅቱን ጠብቆ በአግባቡ መጀመር አለበት ሲባል እንዲሁ ለማለት ብቻ አይደለም።

የሃገራችን ኢኮኖሚ የተመሰረተው በግብርና ላይ ነው። ግብርና ደግሞ ካለ አርሶ አደሩ ዋጋ የለውም። በግብርና ላይ የሚመጣ ለውጥ ነው ሃገራችንን የሚለውጠው ካልን የአርሶ አደሩን አስተሳሰብ ሳንቀይር፣ በሙሉ ልቡ እንዲሰራ ሳናደርግና ከእጅ ወደ አፍ ኑሮ ተላቆ ኪሱ በገንዘብ እንዲሞላ ካላደረግን፣ ጎተራው እንዳይጎድል ካልሰራን ዋጋ የለውም። ለዚህም ነው የአርሶ አደሩን ህይወት መቀየር እና ጥሩ ምርት እንዲመረት ማድረግ የከተማውን የኑሮ ደረጃ የተስተካከለና የሃገሪቱን ዕድገት የተፋጠነ የሚያደርገው።

ስለዚህ አርሶ አደሩ ጉልበትና ውሃን ተጠቅሞ በመሬቱ ላይ የሚያመጣው ለውጥ ወሳኝ በመሆኑ በተቻለ መጠን የምርት ዕድገት የሚጨምርበትን ዘዴ በመቀየስ ያለማቋረጥ መረባረብ ያስፈልጋል። ለውጤቱም የአርሶ አደሩ ድህነት እየተቀረፈ፣ የከተማው ህዝብ የኑሮ ውድነት እየተስተካከለ በአጠቃላይ የሃገሪቱ የምርት ዕድገት እየጨመረ ይሄዳል።

በመሆኑም የዘንድሮው የበልግ መሬት ጥሩ ምርት ስለተገኘ በሚል እንዲሁ እንዳያባክን መስራት ይገባል። አስተማማኝ በሆነ መንገድ ኑሮን ለመቀየር ሌት ከቀን መረባረብ ያስፈልጋል። በውጤቱም በግል፣ በቤተሰብ፣ በመንደር፣ በአጠቃላይ አየአካባቢውና በሃገር ደረጃ በተያዘው መልኩ እድገታችን ይፋጠናል። ተመፅዋችና በድርቅ ተረጂ የመሆናችን ጉዳይ ላይ ክንዳችንን በጋራ ባነሳን ቁጥር ችግሮች በልማት እየተፈቱ ይሄዳሉ። እርዳታ መጠበቅ ይቀራል፣ ከእጅ ወደ አፍ የሆነው ኑሮ ተሻሽሎ የሃገራችን ስም ይቀየራል። ያለንበትን አሳፋሪ የድህነት ገፅታ እንቀይረዋለን፣ ይህን ለአፍታ መዘንጋት አይገባም።

## እኛና እነሱ

# እኛ ለህግ የበላይነት እነሱ ከህግ በላይ ለመሆን

የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 2ኛ ችሎት የቅንጅት ተከሳሾች ያቀረቡትን የዋስትና ጥያቄ ሲመረምር ቆይቶ ባሳለፍነው ሳምንት ውድቅ ማድረጉ ይታወቃል።

ይህንን ተከትሎም ነውጠኞቹ በፍርድ ቤቱና በችሎቱ ዳግም እንደማይዳኙ ለመግለፅሞክረዋል። በዚህና በህግ የበላይነት ጥያቄ ላይ ያለንን አቋም አቅርበናል።

> *«ሁሉም ሰዎች በህግ ፊት እኩል ናቸው፣ በመካከላቸውም ማንኛውም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ በህግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል። በዚህ ረገድ በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ በቀለም፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በማህበራዊ አመጣጥ፣ በሃብት፣ በትውልድ ወይም በሌላ ቋንቋ ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የህግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸው» በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 25 ላይ የተደነገገ።*

ኢህአዴግና በእሱ የሚመራው መንግስት እምነት ከሁሉ በላይ ይህች አገር በህግና በስርዓት የምትመራበት ባህል እንዲዳብር ነው።

ከዚህ እምነትም የመነጨ ህጋዊነትን የማይከተሉ የገዛ ራሱ አመራሮችና አባላትን ካለምህረት የሚቀጣ ከመሆኑም በላይ በህዝብ ምርጫም ቢሆን በስልጣን ላይ የወጣ አካል በማንኛውም ጊዜ በፈፀመው ተግባር ተጠያቂ የሚሆንበትን አሰራር ዘርግቷል።

ይህንኑ ስርዓት ይበልጥ ለማጠናከርም በየደረጃው ግልፅና አሳታፊ የሆነ የግምገማ ስርዓት በማበጀት የተገኙ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በየጊዜው እየፈተሸ አለብኝ የሚለውን ችግር በአደባባይ በመግለፅ ህዝቡ በስርዓቱ ውስጥ የሚታዩትን አዝማሚያዎች ተገንዝቦ የበኩሉን ሚና እንዲጫወት ሲያደርግ ቆይቷል።

የህዝቦች ሉዓላዊነት የሚገለፀው በህገ መንግስቱ መሰረት በሚመርጧቸው ተወካዮችና ህዝቡ በየደረጃው በቀጥታ በሚያደርገው ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ አማካኝነት መሆኑን በመገንዘብ ለምሳሌ በ1992 ዓ.ም ከሻዕቢያ ጋር ጦርነት ውስጥ በነበርንበት ጊዜም የውስጥ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ መገታት የለበትም ከሚለው አቋሙ ተነስቶ ብሔራዊና ክልላዊ ምርጫ እንዲካሄድ በፅናት ተንቀሳቅሶ ተግባራዊ አድርጓል።

ባለፈው ዓመት በተደረገው አገር አቀፍ ምርጫ ሂደት ከሁሉም በላይ አባሎቹን በህጋዊና በፍትሃዊ አሰራር የሚጠፍር መመሪያ በማውጣት ለህግ የበላይነት በፅናት እንደሚሰራ አረጋግጧል።

ከሁሉ በላይ ደግሞ ህግ አውጪው አስፈፃሚውና የዳኝነት አካሉ የየበኩላቸውን ተግባር በነፃነትና በህጋዊ መንገድ የሚወጡበትን አሰራር በመዘርጋት በፅናት ተግባራዊ ሲያደርግ ቆይቷል።

ይህም በኢፌዴሪ ህገ መንግስት በሚከተለው አኳኋን ተደንግጎ ይገኛል።

*«በፌዴራልም ሆነ በክልል የዳኝነት ስልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ ነው፣*

*«በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ የዳኝነት አካል ከማንኛውም የመንግስት አካል፣ ከማንኛውም ባለስልጣን ሆነ ከማንኛውም ሌላ ተፅዕኖ ነፃ ነው፣*

***«ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በሙሉ ነፃነት ያከናውናሉ። ከህግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም»*** *(አንቀፅ 79 ንኡስ አንቀፅ 1-3)*

*መንግስትና ኢህአዴግ ለህጋዊና ዴሞክራሲያዊ ስርአት ባላቸው ቁርጠኛ አቋም በተለያየ መልኩ ጥፋተኛ ናቸው ብለው የሚያቀ ርቧቸውን ተከሳሾች ፍርድ ቤቶች በነፃ እስከመልቀቅ ሲወስኑ፣ የሙስናና የተለያዩ ወንጀሎች ፈፅመዋል ብሎ ያቀረቧ ቸውን ግለሰቦች በነፃ ሲያሰ ናብቷቸው ታይቷል።*

*አንዳንድ ውሳኔዎችን ባያምንባቸውም እንኳን ለህግ የበላይነትና ለዳኝነት ነፃነት ካለው አክብሮት የተነሳ ያለ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ወንጀለኞች ያላቸውን አስሮ ለማቆየት አሊያም የተለያዩ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ለመውሰድ አልሞከረም።*

*በአንፃሩ የሃገራችን ተቃዋሚዎች **«ማንኛ ውም ዜጋ፣ የመንግስት አካላት፣ የፖለቲካ ድርጅቶች ሌሎች ማህበራት እንዲሁም ባለስልጣኖቻቸው ህገ መንግስቱን የማስከበርና ለህገ መንግስቱ ተገዥ የመሆን ሃላፊነት አለባቸው»** የሚለውን የህገ መንግስቱን አንቀፅ 9 ንኡስ አንቀፅ 2 ድንጋጌ በመጣስ በህግ አልዳኝም የሚል አስተሳሰብ በማራመድ ላይ ይገኛሉ።*

*ገና ወደ ፖለቲካ ድርጅትነት በመጡበት ወቅት **«በዚህ ህገ መንግስት ከተደነገገው ውጭ በማንኛውም አኳኋን የመንግስት ስልጣን መያዝ የተከለከለ ነው»** የሚለውን የህገ መንግስቱን አንቀፅ 9 ንኡስ አንቀፅ 3 ድንጋጌ በመጣስ በተለያየ መንገድ በህገ ወጥ አካሄድ የቀሰቀሷቸውን ነውጠኞችና የውጪ አጫፋሪዎቻቸውን በማነሳሳትና በማስፈራራት ስልጣንን ለመጨበጥ እንደሚያልሙ በተደጋጋሚ የተጠቀሰ ጉዳይ ነው።*

*በአገር ውስጥ በአደባባይ ከፈፀሟቸው የማነሳሳት ተግባራት በተጨማሪ በውጪ አገሩ ትም ለአመፅና ለብጥብጥ አስፈላጊው ዝግጅት እንዲደረግ ህግ ተላል ፈው ጥሪ ማስተላለፋቸው የአደባባይ ሚስጢር ነው።*

*ከዚህም አልፈው በሻዕቢያ ከሚደገፈው ኦነግ ጋር በመሆን በወታደራዊ ሃይል ኢህአዴግን ከስልጣን ለማባረር ግልፅና ስውር እንቅስቃሴዎችን ሲያካሂዱ መቆየታቸውም የሚዘነጋ አይ ደለም።*

*ይህ የክህደት ተግባር አልበቃ ብሏ ቸው ለደሃ ህዝብ የሚሰ ጠው ብድርና ዕርዳታ እንዲቋረጥ ተከታታይ ተማፅኖ ሲያቀርቡ ቆይተዋል። በተለያየ መንገድ የመሰረቱትን ግንኙነት በመጠቀምና የሃገሪቷን መልካም ገፅታ በማበላሸት ወደ ስልጣን የሚመጡ እየመሰላቸው ከሚፈፅሙት ከአፍራሽ ድርጊታቸው ዛሬም ሊታቀቡ አልቻሉም።*

*ራሳቸውን ከህግ በላይ የሚያደርጉ እነዚህ የነውጥ ሃይሎች ለበርካታ ዜጎች ህይወት መጥፋት፣ በሚሊዮኖች ለሚቆጠር ንብረት ውድመትና የሃገርን ሰላም በማደፍረስ የፈፀሙትን ተግባር ተራ የፖለቲካ ጨዋታ አድርገው ለማቅረብም እየቃጣቸው ነው።*

*ዴሞክራሲያዊ ስርአትንና አሰራርን የሚሸከም አስተሳሰብ ስለሌላቸው በህገ ወጥ መንገድ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ክብራቸውንና ጥገኛ ፍላጎታቸውን ለማሟላት እየዳከሩ ይገኛሉ።*

*በእኛ እምነት ዴሞክራሲ ካለ ህግ የበላይነት የሚታሰብ አይደለም። በመሆኑም «ጉዳዩ የፖለቲካ ቁማር» ነውና መፍትሄውም በዚያው መንገድ ነው የሚለው ቀልድ ጊዜው ያለፈበት ጉዳይ ይመስለኛል።*

*የሰው ህይወት እየጠፋ፣ ንብረት እየወደመ፣ ሰላምና መረጋጋት እየደፈረሰ የሚደረግ የፖለተካ ጨዋታ ሃላፊነት ከሚሰማው የፖለቲካ ፓርቲና መንግስት የሚጠበቅ ተግባር አይደለም።*

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉት «በቢላዋ ላይ ቀልድ የለም አለች ዶሮ» ነው ጉዳዩ። በሌላ ነገር መቀለድ ይቻላል። በህዝብ ህይወትና ንብረት፣ በሃገር ሰላምና ደህንነት ግን ቀልድ የለም።

በመሆኑም ኢህአዴግንና መንግስትን፤ ህዝብን አነሳስተን እናጠፋቸዋለን ያሉትን አጉራ ዘለሎች የተሻለ አቅም ስላለኝ «ለምሳ ያሰባችሁኝን ለቁርስ ላድርጋችሁ» አላለም። ምክንያቱም ስብዕናውም ሆነ የተፈጠረበት አስተሳሰብ አይፈቅደውምና።

ኢህአዴግ ሁሉን ነገሮች በተቻለ መጠን በትዕግስት ለማለፍ ነው የሞከረው። ፓርላማ አንገባም፣ አዲስ አበባንም አንረከብም ብለው ለመረጣቸው ህዝብ ያላቸውን ንቀት በአደባባይ በገለፁበት ወቅት ተነስቶ እርምጃ ለመውሰድ አልተጣደፈም።

ይልቁንም የያዙት መንገድ የጥፋት መንገድ መሆኑንና እንደማያዋጣቸው ተገንዝበው ወደ ትክክለኛውና ህጋዊ አካሄድ እንዲመለሱ መንግስትና ኢህአዴግ ያቀረቡላቸውን ሰላማዊ መንገድ እንደ ፍርሃት በመጣስ እየተንቀሳቀሱ መሆናቸው ከሁሉም ዜጋ የተሰወረ አይደለም። ስለሆነም ለዳግም ጥፋት የሚሰጥ ዕድል ሊኖራቸው አይገባም።

ዛሬ የፖለቲካ ጨዋታ አድርገው ለመግለፅ የሚሞክሩ የጥፋት ሃይሎች በሰላማዊ መንገድ በበሳል ፖለቲካዊ አካሄድ ወደ ድርድር ግቡ በተባሉበት ወቅት «የምን ድርድር» በማለት እንዳልተሳለቁ ዛሬ ምነው የፖለቲካ መፍትሄ አሰኛቸው።

ለማንኛውም ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉት «ለሁሉም ጊዜ አለው» እናም ህጋዊና ሰላማዊውን መንገድ አሻፈረኝ በማለት በፈፀሙት ተግባር የተዳፈሩት ህግና የሃገሪቷ ህገ መንግስት የዜጎችንና የሃገሪቷን መብቶች ያስከብራሉ ብለን እናምናለን።

አንዳንዶም ካሉት ፍርድ ቤት ውሳኔያቸውን የግድ ይቀበላሉ። የጥፋት ሃይሎች እየሚሸሹ የህግ የበላይነት እየጎለበተ የተያያዝነው ዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ የበለጠ ስሩን እንደሚሰድ ጥርጥር የለንም።

ለዚሁም ተፈፃሚነት በህጋዊ፣ በሰላማዊና በዴሞክራሲያዊ መንገድ ተጠቃሚ የሚሆኑ ዜጎች ሁሉ ለህግ ልዕልና በፅናት ሊቆሙ ይገባል እንላለን።